የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24nd Year No.43
ADDIS ABABA 19th June, 2018

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፭/፪ሺ፲ ዓ.ም

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ገፅ.........፲ሺ፫፻፳፮

## CONTENTS

Regulation No.425 /2018

Electrical and Electronic Waste Management and
Council of Ministers Regulation ..................page

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፭/፪ሺ፲

## የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፪ሺ አንቀጽ ፳ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፭/ ፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ እና ለመለካት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ጨምሮ በኤሌክትሪክ ወይም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል የሚሰራ እና ለተለዋዋጭ ከረንት እንዲሁም ለቀጥተኛ ከረንት የተሰራ መሣሪያ ነው፡

Council of Ministers Regulation No. 425 /201

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON MANAGEMENT AND DISPOSAL OF ELECT AND ELECTRONIC WASTE

This Regulation is issued by the Council of pursuant to Article 5 of the Definition of Powers a of the Executive Organs of the Federal Democratic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article Environmental Pollution Control Proclamation 2008.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Electr Electronic Waste Management and Disposal C Ministers Regulation No. 425 /2018".

### 2. Definition

In this Regulation:

1/ "Electrical and electronic equipment" m equipment which is powered by electric or electromagnetic fields including those the generation, transmission and measur electric currents and electromagnetic field

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 18.35

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ "የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ" ማለት ከጨረራ አመንጪ መሳርያዎች ዉጪ ሁሉም ዓይነት የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ እና የመሳርያ ክፍል ነው፤

፫/ "የተራዘመ የአምራቾች ሀላፊነት" ማለት ማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች አምራች ምርቱን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የመያዝ ሀላፊነት ነው፤

፬/ "አምራች" ማለት ማንኛውም፦

ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በራሱ የንግድ ምልክት በፋብሪካ አምርቶ ለሽያጭ የሚያቀርብ፣ ወይም

ለ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በመገጣጠም ለሽያጭ የሚያቀርብ፤ ሰው ነው፤

፭/ "አስመጪ" ማለት የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስመጣ ሰው ነው፤

፮/ "ተጠቃሚ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን የሚጠቀም ማንኛውም ሰው ነው፤

፯/ "የጅምላ ሻጭ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን ከፋብሪካ ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

፰/ "የችርቻሮ ሻጭ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ከጅምላ ሻጭ ወይም ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

፱/ "በድጋሚ መጠቀም" ማለት ቆሻሻ ያልሆኑ ምርቶች ወይም ክፍሎች ለተሰሩበት አላማ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ማንኛውም አሰራር ነው፤

፲/ "መሰብሰብ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ወደ ቆሻሻ ህክምና ማዕከል ለማጓጓዝ ቆሻሻዎቹን በቅድሚያ በመለየት እና በማከማቸት

2/ "Electrical and electronic waste" means all type electrical and electronic equipment and its p except radioactive equipment, that have discarded;

3/ "Extended producer responsibility" m responsibility of any producer of electrical electronic equipment for environmentally s management of such products;

4/ "Producer" means any person who: -

a) Manufactures electrical and elect equipment under his own brand/ mark; or

b) Assembles electrical and elec equipment for sale;

5/ "Importer" means any person who imports el and electronic equipment into Ethiopia;

6/ "Consumer" means any person using electric electronic equipment;

7/ "Wholesaler" means any person who sells ele and electronic equipment to a retailer after l them from a manufacturer or an importer;

8/ "Retailer" means any person who sells electric electronic equipment to consumers or user buying them from a wholesaler or a manufa or an importer;

9/ "Reuse" means any operation by which prod components that are not waste is used agai the same purpose for which it is conceived

10/ "Collection" means the gathering of electric electronic waste, including the preliminary and preliminary storage of waste for the pu

ማሰባሰብ ነው፤

፲፩/ "የማሰባሰቢያ ማዕከል" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ለማሰባሰብ የተቋቋመ ማዕከል ነው፤

፲፪/ "መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ቁሶችን ከተሰሩበት ዓላማ ዉጪ ለሌላ አገልግሎት እንደገና የመጠቀም ሂደት ነው፤

፲፫/ "መልሶ ጥቅም ላይ የሚያውል" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፬/ "ማደስ" ማለት ያገለገለ ወይም የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ወይም ክፍሎችን መልሶ ለመሸጥ ወይም በድጋሚ ለመጠቀም የሙከራ ፍተሻ፣ የመጠገን፣ የማሻሻል ወይም የማሳደግ አገልግሎት ነው፤

፲፭/ "አዳሽ" ማለት ያገለገለ ወይም የተጣለ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን ወይም ክፍሎች በማደስ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፮/ "መለያየት" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን በመገንጣጠል የተለየው ክፍል ባለበት ሁኔታ ጥቅም ወደሚሰጥበት፣ ወይም በለውጥ ሂደት አልፎ ምርትን ለማምረት የጥሬ ዕቃ ወደሚሆንበት፣ ወይም መወገድ ያለበትአደገኛ ቁስነት የመለየት ተግባር ነው፤

፲፯/ "አወላላቂ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን በማወላለቅ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፰/ "ማከም" ማለት ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ቁሶችን በማውጣት በድጋሚ መጠቀም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ጥቅም እንደማይሰጡ ሲረጋገጥ ማስወገድ ነው፤

፲፱/ "መልሶ ማግኘት" ማለት ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ወይም ክፍሎች ወይም ክፍልፋዮች ቁስ ነገሮችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ሀይልን መልሶ ለማግኘት ማቃጠል ነው፤

of transport to a waste treatment facility;

11/ "Collection center" means a center established t collect electrical and electronic waste;

12/ "Recycle" means reprocessing of an electrical ar electronic waste materials for other purposes othe than their original purpose;

13/ "Recycler" means any person who is engaged i recycling of electrical and electronic waste;

14/ "Refurbish" means functional testing, repairin upgrading or otherwise preparing used discarded electrical and electronic equipment components thereof for resale or reuse;

15/ "Refurbisher" means any person who is engaged refurbishment of used electrical and electron equipment or component;

16/ "Dismantle" means the process of disassembling electrical and electronic equipment into parts th can be reused as they are or that can be used as raw material to make new appliances or th become hazardous material for disposal;

17/ "Dismantler" means any person engaged dismantling of electrical and electronic equipmen

18/ "Treatment" means reuse or recycling of electric waste by recovering useful materials from suc wastes or disposal of electrical and electronic was when it is deemed useless;

19/ "Recovery" means recycling of materials fro electrical and electronic waste or parts and fraction thereof or incineration with energy recovery;

፳/ "አጓጓዥ" ማለት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በየብስ ወይም በባህር ወይም በአየር በማጓጓዝ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፳፩/ "ማስወገድ" ማለት ማንኛውም መልሶ መጠቀም ወይም እንደገና ማግኘትን የማይጨምር ስራ ሲሆን የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማቃጠል ፣ መቅበር ወይም ጥብቅ በሆነ የቆሻሻ መጣያ ማከማቸት ነው፤

፳፪/ "ለአካባቢ ተስማሚ የቆሻሻ አያያዝ" ማለት በአደገኛ ቆሻሻ አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሰው ጤና፣ አካባቢን እና ሀብትን በሚጠብቅ መልኩ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ሁሉንም እርምጃዎችን መውሰድ ነው፤

፳፫/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማንኛውም ክልል ማለት ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፳፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፭/ "ሚኒስቴር እና ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፳፮/ በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ አንድ ተደርገው የተዘረዘሩት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች እና ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ የሚያካትታቸው ሌሎች መሣሪያዎችን በሚያመርቱ ፣በሚያከፋፍሉ፣በሚቸረችሩ፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡ፣ በሚያጓጉዙ፣ በማሰባሰቢያ ማዕከሎች፣ በአዳሾች፣ በአወላላቂዎች ወይም መልሶ ጥቅም ላይ በሚያውሉ እና በተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

20/ "Transporter" means any person engaged i transportation of electrical and electrical was land, air or sea;

21/ "Disposal" means any operation which doe lead to recycling or recovery and inc incineration and deposition of electrical electronic waste in secured landfill;

22/ "Environmentally sound management of wa means taking all practicable steps to ensure hazardous waste are managed in a manner v protects human health and the environment ag the adverse effects which may result from waste and to save resources;

23/ "Region" means any region of the Fe Democratic Republic of Ethiopia referred Article 47(1) of the Constitution of the Fe Democratic Republic of Ethiopia and, incl the Addis Ababa and Dire Dawa administrations;

24/ "Person" means any natural person or juri person;

25/ "Ministry and Minister" means the Ministry Minister of Environment, Forest and Cli Change, respectively;

26/ Any expression in the masculine gender incluc the feminine.

## 3 .Scope of Application

This Regulation shall apply to producers, distribu retailers, importers, transporters, collection centers furbishers, dismantlers, recyclers and consumers electrical and electronic equipment listed under ANN ONE of this Regulation and any other appliance that be added to the list by the Ministry in a Directive iss under this Regulation.

## ክፍል ሁለት

## የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ

### ፬. የቆሻሻ አያያዝ ቅደም ተከተል

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚከተሉት የቆሻሻ አያያዝ ደረጃዎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡-

፩/ የቆሻሻ ምንጮችን መቀነስ፣

፪/ ቆሻሻን ማደስ እና በድጋሚ መጠቀም፣

፫/ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል፣

፬/ ቆሻሻን ማስወገድ፡፡

### ተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት

፩/ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ምንጮችን ለመቀነስ እና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ በድጋሚ መጠቀምን፣ ማደስን እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን ለማጠናከር ማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ አምራች፣ ጅምላ ሻጭ፣ ቸርቻሪ ወይም ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

፪/ የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት የሚከተሉትን ኃላፊነቶች ያስከትላል፡-

ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች በሚመረቱበት ወቅት የሚመነጨ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን ማሰባሰብ እና ቆሻሻዎቹን ለማደሻ፣መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ወይም ለማስወገጃ ማዕከሎች ማስተላለፍ፣

ለ) የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ማሰባሰብ ወይም ከሸማቾች መልሶ መቀበል እና ፍቃድ ለተሰጣቸው የማደሻ፣ የማወላለቂያ እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ

## PART TWO

## MANAGEMENT OF ELECTRICAL AND ELECTRONIC WASTE

### 4. Hierarchy of Waste Management

To minimize the environmental impacts of electrical a electronic waste, the following waste management hierarchy shall be applied;

1/ Reduction of waste generation;

2/ Refurbishing and reuse of waste;

3/ Recycling of waste;

4/ Disposal of waste.

### 5. Extended Producer Responsibility

1/ In order to reduce sources of electrical and electr waste generation and to strengthen the re refurbishing and recycling of electrical and electr waste, any electrical and electronic equipn producer, wholesaler, retailer or importer shall h extended producer responsibility.

2/ The extended producer responsibilities shall entai the following responsibilities;

a) Collection of electrical and electronic w generated during the manufacture electrical and electronic equipment channelizing same for recycling or dispo

b) Collection of electrical and electronic w generated from the end of life of products or take back system, and to en that such electrical and electronic wast channelized to registered refurbishin

ማዕከሎች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለመያዝ እና ለማስወገድ የሚያስፈልግ ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል አደረጃጀት መዘርጋት እና በገንዘብ መደገፍ፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ የአምራቾች መዝገብ እና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዝርዝር ቆጠራ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡

፬/ ማንኛውም አምራች ፣ ጅምላ ሻጭ እና ቸርቻሪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዝርዝር መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን መዝገቡም ሚኒስቴሩ ለሚያደርገው ምርመራ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፡፡

**የተጠቃሚ ኃላፊነት**

ተጠቃሚዎች የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰብሰቢያ ማዕከሎች ወይም ቆሻሻዎቹን የሚሰበስቡ ሰዎች መረከባቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

**ቆሻሻን ስለመሰብሰብ**

፩/ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ማዕከልን ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ማዕከልን ለመክፈት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

ሀ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አሰባሰብ ከሌሎች ዓይነት ቆሻሻ ተለይቶ መካሄዱን የማረጋገጥ፣

ለ) የቆሻሻው ዝቃጭ እንቅስቃሴ ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን የማረጋገጥ፣

dismantling or recycling centers;

c) Financing either individually or colle and organizing a system to meet the involved in the environmentally management disposal of electrica electronic waste.

3/ The Ministry shall maintain the register of pro and inventory of electrical and electronic waste.

4/ Any producer, wholesaler and retailer shall records of the electrical and electronic waste anc records shall be accessible for scrutiny by the Mi

**6. Responsibilities of Consumers**

Consumers shall have responsibility to ensure tha electrical and electronic waste are handed ove collection centers or to persons entitled to collec collection centers.

**7. Collection of Wastes**

1/ Any person seeking to open a collection cente electrical and electronic wastes shall su application to the Ministry, secure a certificat competence and get registered.

2/ The person who secured a certificate of compet from the Ministry to open a collection center electrical and electronic waste shall have the follo responsibilities:

a) The collection of electrical and electronic w shall be done separately from other type wastes;

b) The downstream traceability and movemen the waste;

ሐ) የተሰበሰበው የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ፍቃድ ወደተሰጠው ማወላለቂያ፣ማደሻ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ተቋም እስከሚወሰድ ድረስ ማንም ሰው በማይደርስበት እና ምንም ሊበክል በማይችልበት ሁኔታ መከማቸቱን የማረጋገጥ፣

መ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻው በሚሰበሰብበት ፣ በሚከማችበትም ሆነ በሚጓጓዝበት ወቅት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ምንም አይነት ጉዳት የማያመጣ መሆኑን እና

ሠ) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማሰባሰቢያ ቦታ ለተጠቃሚዎች በቅርበት የሚገኝ መሆኑ እና የሚሰጠው አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ማስተዋወቁ የማረጋገጥ፡፡

**ሻሻ ስለማወላለቅ**

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ የማወላለቂያ ማዕከልን ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን በማወላለቅ ስራ ላይ ለመሰማራት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የማወላለቅ ሂደቱ በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያደርስ መሆኑን፣

ለ) የማወላለቁ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ተለያይተው ሊቀመጡ የሚችሉበት ቦታ ወይም ክፍል የተዘጋጀ መሆኑን፣

፫/ ማንኛውም የማወላለቂያ ማዕከል የሚከተሉትን መረጃዎች መዝገብ መያዝና መዝገቡም ለሚኒስቴሩ

c) The electrical and electronic wastes collected stored in a manner that ensures that nobo reaches them and that they pollute nothing they are sent to the authorized dismantli refurbishing or recycling center;

d) No damage is caused either to human health or the safety of the environment during collecti storage or transportation of the electrical electronic wastes.

e) Ensure that electrical and electronic collection is located within a reasonable proximity consumers, and their services should be w advertised.

**8. Dismantling of Waste**

1/ Any person seeking to set up a dismantling center electrical and electronic waste shall submit applicat to the Ministry, secure a certificate of competence get registered.

2/ Any person that secured a competence of certific from the Ministry to engage in dismantling items electrical and electronic equipment shall have following responsibilities;

a) The dismantling processes do not have adverse effect on human health or on safety of the environment;

b) The place or room to the dismant electrical and electronic wastes are rea available.

3/ Any dismantling centre shall maintain the follow records and shall make accessible for scrutiny by

ለምርመራ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡-

ሀ) ወደ ማዕከሉ የመጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ዓይነት እና ክብደት፤

ለ) ከማዕከሉ የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ክፍልፋዮች ዓይነት እና ክብደት

ሐ) ከማዕከሉ የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ክፍልፋዮች መዳረሻዎችን የሚያሳይ ማስረጃ፡፡

ሻን በድጋሚ ጥቅም ላይ ስለማዋል

ጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የታቀዱ የኤሌክትሪክና ክትሮኒክ ቆሻሻ መስራት እንደሚችሉ በአዳሽ ተቋማት ካይነት በተገቢው ሊፈተሹ እና ውጤቱም ሊመዘገብ ል፡፡

ን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚኒስቴሩ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የምዝገባ ግዴታዎችን የማሟላት፤

ለ) መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የተገኙ የተለያዩ ቁሶችን ብዛት የሚያሳይ ሰነድ የመያዝ፤

ሐ) መዛግብቱን ሁሉ ለሚኒስቴሩ ግልጽና ተደራሽ የማድረግ፤

መ) መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ዝቃጮች ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ የቆሻሻ አያያዝ ዘዴ እንዲወገዱ የማድረግ፡፡

Ministry:-

a) Types and weights of electrical a electronic wastes received;

b) Types and weights of fraction of electric and electronic wastes dispatched;

c) Evidence of fraction of the destinatio of dispatched wastes.

**9. Reuse of Wastes**

Electrical and electronic waste destined for reuse sha properly be tested by the re-furbishers for the functionality and the results are recorded.

**10. Recycling of Wastes**

1/ Any person seeking to engage in recycling electrical and electronic waste shall submit application to the Ministry, secure a certificate of competence and get registered.

2/ Any person that secured a competence certificat from the Ministry pursuant to sub-article (1) of thi Article shall have the following have the followin responsibilities:

a) Compliance with the terms and condition of registration;

b) Documentation of quantities of the variou output materials from recycling processes;

c) Made accessible records to the Ministry;

d) That the hazardous residues generatec during the recycling process are disposed of in an environmentally sound waste management.

**ሻን ስለማደስ**

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን በማደስ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የምዝገባ ግዴታዎችን የማሟላት፣

ለ) መዛግብቱን ሁሉ ለሚኒስቴሩ ግልጽና ተደራሽ የማድረግ፤

ሐ) በማደስ ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ዝቃጮች ለአካባቢ ተስማሚ ቆሻሻ አያያዝ ዘዴ እንዲወገዱ የማድረግ፡፡

**ሻ ላይ መለያ ስለማድረግ**

ጋሚ በጥቅም ላይ የዋሉ፣የታደሱ እና መልሶ ጥቅም የዋሉ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በሙሉ ጋሚ ጥቅም ላይ እንደዋሉ፣ እንደታደሱ ወይም ሰው ጥቅም ላይ የዋሉ ምርቶች መሆናቸውን እና ሳቸው ወይም መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ረጋቸውን ተቋም ማንነት የሚገልጽ የፅሁፍ ታወቂያ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች በግልጽ በቋሚነት መለጠፍ አለባቸው፡፡

**ሻን መልሶ በጥቅም ላይ ከማዋል በፊት ማከምና አያያዝ**

የማከም ስራ ከተደረገለት በኋላ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያን በድጋሚ መጠቀም እንደማይቻል ከታመነ ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት አግባብነት ባለው የቆሻሻ ማከማቻ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

በአያያዝ ጉድለት ሳቢያ ሊደርስ የሚችል የዕቃ መሰበርን እና ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ቁሶች መለቀቅ ጠንቅን በተቻለ መጠን ለመቀነስ በቂ

**11. Refurbishing of Wastes**

1/ Any person seeking to engage in refurbishing of electrical and electronic waste shall submit application to the Ministry, secure a certificate of competence and get registered.

2/ Any person that secured a certificate of competence from the Ministry pursuant to sub-article (1) of this Article shall have the following responsibilities:

a) Compliance with the terms and conditions of registration;

b) Made accessible records to the Ministry;

c) The hazardous residues generated during the refurbishing process are disposed of in an environmentally sound waste management.

**12. Labeling of Wastes**

All electrical and electronic waste that is reused refurbished or recycled shall be clearly and permanentl labeled with a written notification both in Amharic an English Languages that it is reused, refurbished ( recycled product and the identity of the refurbishing ( the recycling facility.

**13. Treatment and Management of Waste befo Recycling**

1/ After conducting treatment if an item of electric and electronic equipment is deemed un-reusable, shall be kept in an appropriate waste storage.

2/ During storage, the risks of breakage and potent exposure to substances of concern from improp

ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

፫/ በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከልነት የተመዘገበው ድርጅት ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለማስወገድ እንዲሁም አደጋ ለመከላከል የሚያስችል ዘዴን በሚመለከት ለሠራተኞቹ በቂ ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሻን መለየት እና በጊዜያዊነት ማከማቸት

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ለተጨማሪ ምርመራ ተለይተው መከማቸት አለባቸው፡፡

የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሚያሟሉ ስፍራዎች ሊገኙ ይገባል:

ሀ) የማከማቻ ማዕከሉ ለእሳት ማጥፋትና ለሌሎች አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች አመቺ መሆኑ፣

ለ) የማከማቻ ማዕከሉ ለጎርፍ ያልተጋለጠ መሆኑ፣

ሐ) የማከማቻ ማዕከሉ በመሬት ላይ እና በመሬት ውስጥ የሚገኝ የውሀ ክምችት ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ፡፡

ማንኛውም ያልተፈቀደለት ሠራተኛ ወይም ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው የማከማቻ ሥፍራ መግባት አይፈቀድም።

የማከማቻ ተቋሙ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ መከማቸታቸውን የሚገልፁ ምልክቶችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) ላይ የተገለፁት ምልክቶች በቅርብ ርቀት ሊታዩ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

የማከማቻ ቦታዎች ለኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ መለዋወጫዎች፣ መልሶ ጥቅም ላይ

handling shall be minimized.

3/The owner or manager of the recycling center shal ensure provision of sufficient training to all the staf members to avoid possible risks and on mechanism of their prevention.

## 14. Sorting and Temporary Storage of Waste

1/ Electrical and electronic waste shall be sorted for furth examination.

2/ A storage center shall be located in places that meet tl following criteria:

a) The center shall be readily accessib for firefighting and other emergen situations;

b) The storage center is not subject flooding;

c) The storage center shall not cause a damage to the quality of surface wa and ground water.

3/ There shall be no entry of any unauthori: personnel or individual into the storage cer specified under sub-article (1) of this Article.

4/ A storage center shall bear signs indicating t electrical and electronic waste is stored therein.

5/ The signs that are mentioned under sub- Article of this Article shall be of such design as to legible from a reasonable distance.

6/ Storage area shall be assigned and marked for sp of electrical and electronic equipment, ou

ለሚውሉ ክፍልፋዮች እና ክፍሎች፣ ለሚወገዱ ክፍልፋዮች እና ክፍሎች እና ለማደስ የሚውሉ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ተብለው መመደብ አለባቸው።

የማከማቻ ማዕከሉ ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ በማከማቻ ማዕከሉ ለመከማቸት የገቡ ወይም የወጡ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አይነት፣ የተከማቹበት ስፍራ፣መጠን እና ቀን የሚገልፅ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

ቆሻሻን ማጓጓዝ

/ በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እና መመዝገብ አለበት፡፡

የማንኛውም የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አጓጓዥ ቆሻሻው በድጋሚ በጥቅም ላይ ሊውል የመቻል ሁኔታን እና ቀጣይ ህክምናን በማያናጋ መንገድ ማጓጓዝ አለበት።

/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ክልል ተሻጋሪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ ማጓጓዝ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊያገኝ የሚችለው ከቆሻሻው መዳረሻ ክልል የአካባቢ ጥበቃ ተቋም በዝውውሩ መስማማቱን በጽሑፍ ሲገልጽ ብቻ ይሆናል፡፡

የቆሻሻ አወጋገድ

፩/የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ እንዲወገዱ የሚደረጉት በድጋሚ የመጠቀም፣የማደስ እና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አማራጮች ሁሉም ተሞክረው ከተሟጠጠ በኋላ ብቻ ነው፡፡

፪/ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በጥብቅ የቆሻሻ መጣያ ቦታ ወይም በማቃጠል እና ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በሚወሰኑ ቴክኖሎጂዎች መወገድ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

. የሙያ ደኅንነት፣ጤንነትና የሥራ አካባቢ

፩/ ማንኛውም በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ

fractions and components to be recycled, fractio and components to be disposed, and devices a components to be refurbished.

7/ The owner or manager of a storage center sh maintain records indicating the date, type, locati and quantity of electrical and electronic waste t was brought into or removed from the center.

**15. Transportation of Waste**

1/ Any person seeking to engage in the transportation electrical and electronic waste shall submit application the Ministry, secure a certificate of competence and registered.

2/ The transportation of any electrical and electronic wa shall be in a manner that does not affect the reusability subsequent treatment of the waste.

3/ Any trans-regional transportation of electrical electronic waste within Ethiopia may be permitted by Ministry only when the environmental protection or in the destination Regional State has agreed on transfer of the waste in writing.

**16. Disposal of Waste**

1/ The electrical and electronic waste disposal shall be conducted when all available options of re refurbishment and recycling have been exhausted.

2/ Electrical and electronic waste shall be dispose landfilling or incineration and any other technolo that may be determined by the Ministry in a Dire issued under this Regulation.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**17. Occupational Safety, Health and Wor Environment**

1/ Any facility engaged in electrical and elect

አያያዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም የሠራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት በሚገባ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡

፪/ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ የተደነገገው የሙያ ደኅንነት፣ጤንነትና የሥራ አካባቢ መስፈርቶች በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

፲፰.የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት

የዚህን ደንብ ድንጋጌ መጣስ አግባብ ባላቸው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ፣ ድንጋጌዎች እና በሌሎች ሕጎች መሠረት የወንጀልእና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት ያስከትላል፡፡

፲፱.ውክልና የመስጠት ሥልጣን

ሚኒስቴሩ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ከኃላፊነቶቹና ከተግባሮቹ በከፊል ለሌሎች መሥሪያ ቤቶች በውክልና ይሠጣል፡፡

፳.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፩.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

አብይ አሕመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

waste management shall take the necessary measure to safeguard adequately the health and safety of the workers.

2/ The occupational health and safety requirements provided under the Labor Proclamation shall be applicable for persons engaged in electrical and electronic waste management disposal activities.

**18. Criminal and Civil Liability**

Any violation of the provisions of this Regulation shall entail criminal and civil liability in accordance with the appropriate provisions of the Pollution Control Proclamation and other laws.

**19. Power of Delegation**

The Ministry may delegate some of its powers and duties, as it may be deemed appropriate, to other agencies.

**20. Power to Issue Directives**

The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

**21 . Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa, on the 19th Day of June, 2018.**

**ABIY AHMED (PHD.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## አባሪ አንድ

**የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የሚከተሉት የሚጨምር ሆኖ በእነዚህ ብቻ ግን የተወሰነ አይደለ**

| | |
|---|---|
| | **ትላልቅ የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** |
| 1 | ማቀዝቀዣዎች |
| 2 | የአየር መቀት ማመጣጠኛ መሳሪያዎች |
| 3 | የልብስ ማድረቂያዎች |
| 4 | የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች |
| 5 | የኤሌክትሪክ ምድጃዎች |
| 6 | የሰሀን ማጠቢያ ማሽኖች |
| 7 | የኤሌክትሪክ ማሞቂያ መሳሪያዎች |
| 8 | የማይክሮዌቭ ምድጃ እና ሌሎች |
| | **ትናንሽ የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች** |
| 1 | ቫኪዩም ክሊነሮች |
| 2 | የምንጣፍ ማፅጃ |
| 3 | የልብስ ስፌት እና የሽመና መሳሪያዎች |
| 4 | የልብስ መተኮሻ ማሽኖች |
| 5 | መጥበሻዎች |
| 6 | የቡና ማሽኖች |
| 7 | የቡና መፍጫዎች |
| 8 | የኤሌክትሪክ ቢላዎች |
| 9 | የፀጉር መቁረጫ፣ የፀጉር ማድረቂያ፣ የጺም መላጫ፣ የማሳጅ እና ሌሎች የሰውነት መጠበቂያ መሣሪያዎች ሌሎች |

## ANNEX ONE

## ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENT INCLUDES, BUT NOT LIMITTED, TH FOLLOWING

| LARGE HOUSEHOLD ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | REFRIGERATORS |
| 2 | AIR CONDITIONER APPLIANCES |
| 3 | CLOTHES DRYER |
| 4 | WASHING MACHINES |
| 5 | ELECTRIC STOVES |
| 6 | DISHWASHING MACHINES |
| 7 | ELECTRIC HEATING APPLIANCES |
| 8 | MICROWAVE OVENS AND OTHERS |

| SMALL HOUSEHOLD ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | VACUUM CLEANERS |
| 2 | CARPET SWEEPERS |
| 3 | APPLIANCES USED FOR SEWING AND WEAVING |
| 4 | IRONING MACHINE |
| 5 | FRYERS |
| 6 | COFFEE MACHINES |
| 7 | COFFEE GRINDERS |
| 8 | ELECTRIC KNIVES |
| 9 | APPLIANCES FOR HAIR- CUTTING, HAIR DRYING, SHAVING MACHINE, MASSAGE AND OTHER BODY CARE APPLIANCES AND OTHERS |

| | |
|---|---|
| | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የቴሌኮሚዩኒኬሽን<br>የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 1 | ሚኒ ኮምፒዩተር |
| 2 | ሜይንፍሬም ኮምፒዩተር |
| 3 | የግል ኮምፒዩተሮች (ሴንትራል ፕሮሰሲንግ፣ ማውስ፣ ስክሪን እና ኪቦርድ ጨምሮ) |
| 4 | ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች (ሴንትራል ፕሮሰሲንግ፣ ማውስ፣ ስክሪን እና ኪቦርድ ጨምሮ) |
| 5 | ፕሪንተሮች |
| 6 | ኖትፓድ ኮምፒዩተሮች |
| 7 | የኮፒ ማሽኖች |
| 8 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ታይፕ ራይተር |
| 9 | የኪስ እና የጠረጴዛ የሂሳብ መሳሪያዎች |
| 10 | የመረጃ ማሰባሰቢያ እና ማከማቻ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 11 | ቴሌክስ |
| 12 | ስልኮች |
| 13 | ተንቀሳቃሽ ስልኮች |
| 14 | ገመድ አልባ ስልኮች እና ሌሎች |
| | የተጠቃሚ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 1 | ሬድዮ |
| 2 | ቴሌቪዥኖች |
| 3 | የቪዲዮ ካሜራዎች |
| 4 | የቪዲዮ መቅጃዎች |
| 5 | ሀይ ፋይ መቅጃዎች |
| 6 | የኦድዮ አምፕሊፋየሮች |
| 7 | የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| | የመዝናኛ የስፖርት የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 1 | ቪዲዮ ጌም እና አክሰሰሪዎቹ |
| 2 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ አሻንጉሊቶች |
| 3 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ የስፖርት መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| | የህክምና የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች |
| 1 | የራዲዮ ቴራፒ መሳሪያዎች |
| 2 | የካርዲዮሎጂ መሳሪያዎች |
| 3 | የዳያሊሲስ መሳሪያዎች |
| 4 | የላቦራቶሪ መሳሪያዎች |
| 5 | ህመምን ወይም የአካል ጉዳትን ለማወቅ፣ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ለማከም እና ለመቀነስ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እና ሌሎች |

| INFORMATION TECHNOLOGY AND TELECOMMUNICATIONS EQUIPMENT INCLUDES THE FOLLOWIN | |
|---|---|
| 1 | MINICOMPUTER |
| 2 | MAINFRAMES |
| 3 | PERSONAL COMPUTER (CENTRAL PROCESSING UNIT, MOUSE, SCREEN AND KEYBOARD INCLUDED) |
| 4 | LAPTOP PERSONAL COMPUTER (CENTRAL PROCESSING UNIT, MOUSE, SCREEN AND KEYBOARD INCLUDED) |
| 5 | PRINTERS |
| 6 | NOTEPAD COMPUTERS |
| 7 | COPYING MACHINES |
| 8 | ELECTRICAL AND ELECTRONIC TYPEWRITERS |
| 9 | POCKET AND DESK CALCULATORS |
| 10 | ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENT FOR THE COLLECTION AND STORAGE OF INFORMATION |
| 11 | TELEX |
| 12 | TELEPHONES |
| 13 | MOBILE TELEPHONES |
| 14 | CORDLESS TELEPHONES AND OTHERS |

| CONSUMER ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | RADIO |
| 2 | TELEVISIONS |
| 3 | VIDEO CAMERAS |
| 4 | VIDEO RECORDERS |
| 5 | HI-FI RECORDERS |
| 6 | AUDIO AMPLIFIERS |
| 7 | MUSICAL INSTRUMENTS AND OTHERS |

| LEISURE AND SPORTS ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | VIDEO GAME AND ACCESSORIES |
| 2 | ELECTRICAL AND ELECTRONIC TOYS |
| 3 | ELECTRICAL AND ELECTRONIC SPORTING EQUIPMENT AND OTHERS |

| MEDICAL ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | RADIOTHERAPY EQUIPMENT |
| 2 | CARDIOLOGY EQUIPMENT |
| 3 | DIALYSIS EQUIPMENT |
| 4 | LABORATORY EQUIPMENT |
| 5 | OTHER APPLIANCES FOR DETECTING, PREVENTING, MONITORING, TREATING, ALLEVIATING ILLNESS OR DISABILITY ANDOTHERS. |

| | |
|---|---|
| የልኬት ፣የክትትል እና የቁጥጥር የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች | |
| 1 | የጭስ ዲቴክተር |
| 2 | የእሳት ዲቴክተር እና የአደጋ ምልክት |
| 3 | የሙቀት መቆጣጠሪያዎች |
| 4 | ቴርሞስታትስ |
| 5 | በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለክትትል እና ለቁጥጥር አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች እና ሌሎች |
| ብርሀን አመንጪ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች | |
| 1 | ፍሎረሰንት አምፖሎች |
| 2 | ኮምፓክት ፍሎረሰንት አምፖሎች |
| 3 | ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ፕሬሸር ሶድየም አምፖሎች |
| 4 | ኤል.ኢ.ዲ አምፖሎች እና ሌሎች |
| አውቶማቲክ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ዲስፔንሰር | |
| 1 | የትኩስ መጠጦች አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 2 | የቀዝቃዛ የጠርሙስ ወይም የጣሳ አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 3 | ለገንዘብ ማውጫ የሚሆን አውቶማቲክ ዲስፔንሰር |
| 4 | ማንኛውንም ዓይነት ምርት ሊሰጡ የሚችሉ አውቶማቲክ መሣሪያዎች እና ሌሎች |

| MONITORING AND CONTROL ELECTRICAL AND ELECTRONIC EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | SMOKE DETECTOR |
| 2 | FIRE DETECTION AND ALARM SYSTEM |
| 3 | HEATING REGULATORS |
| 4 | THERMOSTATS |
| 5 | OTHER MONITORING AND CONTROL INSTRUMENTS USED IN INDUSTRIAL INSTALLATIONS AND OTHERS |

| LIGHTING EQUIPMENTS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | FLORESCENT LAMPS |
| 2 | COMPACTED FLORESCENT LAMPS |
| 3 | HIGH AND LOW-PRESSURE SODIUM LAMPS |
| 4 | LED LAMPS AND OTHERS |

| AUTOMATIC DISPENSERS INCLUDES THE FOLLOWING | |
|---|---|
| 1 | AUTOMATIC DISPENSERS FOR HOT DRINKS |
| 2 | AUTOMATIC DISPENSERS FOR COLD BOTTLES OR CANS |
| 3 | AUTOMATIC DISPENSERS FOR MONEY |
| 4 | ALL APPLIANCES WHICH DELIVER AUTOMATICALLY ALL KIND OF PRODUCTS AND OTHERS |